# ኃያል ኃይል የኢዮብ ሞራል

ገድሉ መታፈሪያ- በፀጋዬ ቤት

እኛ ስንታመም እንላለን......."አቤቱ ማረኝ ጌታዬ
እግዚኦ ማኸረነ-ክርስቶስ....ጊዜ የሌለህ አንድዬ
ምነው አረዘምከው ሌሊቱን......ምነው ከበደ አበሳዬ
ምነው ሩሕ አጥንቴን ወግሮ፤ ልብሴ ራሰ በእንባዬ፤
ምነውስ ሕዝቤ ታሰረ!....በዘመናት ሰንሰለት፣
ቀናት በተፈራረቁ ቁጥር...እንዳበባ የመፀው ሥልት"፡፡

የባሰ አታምጣብኝ ብሎ... ኢዮብ ሲልጥ ቆዳውን
ያችን ቀን ረግሞ ላሳጣት፣ ከቀናት ሁሉ የናቃትን
እርሷም መከራን ትሸከም ዘንድ፣ ለበጎነት የቀመራት
መሬት በጸሃይ ዞራ.....ቀንና ፅልመት ያደላት
አእጋረ-ፀሓያትን የሠራ፤ አልሻዳይ ነው የፍጡር አባት፡፡

ዳግመኛም ክፉ ወሬ ስንሰማ.....ሠራዊት ከቶ አገር ሲናጥ
ሰው እርስ በርሱ ሲባላ....የደመኛ ጥርስ ብረት ሲቆርጥ
ያኔ ነው መስገድ ያለብን......ጎማማቱ ሲያይሉብን
ሸክማችን ከብዶ ሲደፋን.....መላዕክት ሁሉ ሲርቁን፡፡

የአለም አዳኝ መድኃኒት........ክርስቶስ በኃይል የጮኸው
"ላማ ሰበቅታኒ" ብሎ......ራሱን ካንገቱ የደፋው
የሥጋን ድክመት ለማስተማር ነው...... ጽናት እንዲያበረታው፤
እናም በዚህ ትንሳኤ.....ክርስቶስ ባረገበት
አባቱ ኢዮብን ወዶ...ለሰጠው እጥፍ ሽልማት
እያመማችሁ በመቻል......ችግራችሁን ሁሉ ተወጡት
ሁሉም ለበጎ እንደሆነ.....ጭለማን በብርሃን ሻሩት
እንደናቶች አባቶቻችሁ....የጽናትን ካባ ልበሱት፤

በመቻቻል ይቅርባይነት፣ ለኢትዮጵያ ሰላም መግቢት
ለሕፃናት ወተት አጠጡ.....ለሕዝባችን ዳቦ ስጡት፡፡
"ዓይን ካለቀሰ" አበው....."እምባ አይገድም" እንዲሉ
ትንሳኤያችን ቅርብ ነው....ልባችን ከነፃ በውሉ፤
ግን የፍልስፍና ካቴና፤ ጠፍሮ ከያዘን ፌሮው
ቂመኝነት ካስነከሰን.....መንጋጋችንን ከቆለፈው
ልናመልጥ አንችልም ከቶ....ከጥፋቱ ከሰቆቃው፣
<u>አዎ ይቻላል</u> በይቅርታ.....ኩነኔ በፅድቅ እንዲሻር
ኀራዴ ማረሻ እንዲሆን.....ተኩላ ከበግ እንዲያድር፡፡

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፡፡